ሐምሌ 3 ቀን 2002 ዓ.ም

# ብልጦች የማይሄዱበትን መንገድ፣ ሞኞች ይሮጡበታል!

## ትዝበት

ከአያልነሽ

አንዳንዴ ለምን እንደሆን በማይገባ ሁኔታ የእኔ ቢጤዎችን "እንዲያስተምሩ" የሚጋበዙ ሰዎቻችን፣ አሁን በተጨባጭ የምንገኝበት ሁኔታ ሌላ ሆኖ እያለና፣ እንዲሁም ሐገራችንንና ሕዝብባችንን ወደ መቀመቅ ለመከተት በዝግጅትና በተጠንቀቅ ላይ ያለ ጠላት ፊት ለፊታችን ተንሰራፍቶ በሚገኝበት ሁኔታ፣ ወቅት እየጠበቁ አወዛጋቢ ጉዳዮችን ወደፊት በማምጣት በእንቶ ፈንቶ ንትርክ ውስጥ እንድንገባ የሚሹ ሰዎች አሉ። አጋጣሚና ሁኔታ እየጠበቁም ራሳቸውን የጉዳዩ ማዕከል በማድረግ፣ የሰውን ትኩረት ለማግኘትና ለመሳብ፣ በየአጋጣሚው የሚሰነቀሩ መድረክ ፈላጊዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው። እነኝህ ሰዎቻችን ታዲያ *"ለሀገራችን ኢትዮጵያ መፍትሔ ለማፈላለግ ነው"* በሚል አማላይና ማራኪ ቃል ላይ ይንጠለጠሉና፣ የሰውን ሁሉ ትኩረት ሊሰርቁ ከወዲያ ወዲህ ሲራወጡ ይስተዋላሉ። እናም ዛሬ ከቆመንበት መሬት ላይ በድንገት ይነቅሉንና፣ እነርሱ ሲፈልጉ፣ እኛን ሁሉ ወደኋላ አርቀው በመመለስ፣ በዛሬው የሀገራችንንና የህዝባቸን ጠላት ላይ እንዳናተኩርና እንዳናይ ለማድረግ፣ ብዙ፣ ብዙ ይጓዛሉ። የሚገርመው ደግሞ የሚታይን አስጥለው የማይታይን የሚያሲይዙ፣ የሚጨበጥ ነገር አስለቅቀው የማይጨበጥ ጉም የሚዘግኑና የሚያዘግኑ መሆናቸውን ስናስብ፣ እውነትም ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር የሚታዘንላት ለመሆኗ እውነት አለው። እስከ ትናንትናው ቅርብ ቀን፣ ላንቃቸው እስኪደረቅ ድረስ መድረክ እየፈለጉ ደጋግመው የሚጮሁለት "ህብረት፣ ህብረት" የሚል መዝሙራቸውን አሁን፣አሁን ያቆሙና የተውት ይመስላል። ከዚህ የ*"ህበረት"* ጩኸታቸው ጋር አያይዘውም፣ እንዲህ ሲሉም ተደምጠው ነበር - በአሁኑ ጊዜ "ያለፈን ነገር አናንሳ፣ እርስ በርስም አንነካካ፣ ሁሉም ሰው ዓይኑን ወደ ዋናው ጠላታችን ወያኔ ላይ ያድርግ በማለት ለአንድ ሰሞን ሲነግሩንና ሲያስተምሩንም ቆይተዋል። እናም ይህንን እያሉን ከረሙና ዛሬ ደግሞ ሁሉም ነገር እንዳሰቡትና እንደጠበቁት አልሄድና አልሆን ሲላቸው፣ የሚናገሩበት አርዕስት አለቀ ወደ ሌላ ነገር መንጠላጠል ጀምረዋል። በመሆኑም የሚያወሩት ነገር ስለጠፋ *"ሥራ ከመፍታት ልጇን ላፋታት"* ዓይነት፣ እንደገና ዛሬ ወደ ኋላ በመመለስ የ40 ዓመቱን የትግል ጉዞ እንገምገም በሚል "ልኂቃን"-ን ጋብዞ የጀርመን ድምፅ ራዲዮ ጋዜጠኛ ነጋሽ መሐመድ፣ ማወያየት ይዟል። በሚያስገርም ሁኔታ አሁን ህዝባችን በአንድ ላይ ቆሞ፣ ትኩረቱንም በሙሉ አገሩን ሊያጠፋ በሚያቆበቁበው ጠላቱ ላይ ባተኮረበትና ዕይታውን በሙሉ በዚያ ላይ ባደረገበት ወቅት፣ ይህንን የጠራና ግልፅ የሆነ ዕይታውን ለማደፍረሰና ዓይኑን ከዕይታው እንዲነቅል ለማድረግ ብዙ፣ ብዙ ሲደክሙ ይታያሉ።

ትናንት በመከራው ላይ ተረማምዶ፤ የመከራውም የመጀመሪያ ሰለባና የግፉ ተጋፋጭ ለነበረው ህዝባችንም፣ ያን ያለፈበትንና የተጓዘበትን የራሱን የታሪክ ጉዞ፣ ብሎም በዚያ ጉዞ ውስጥ መከራና ፍዳውን ሲይስቆጥሩት የነበሩ አገዛዞችን አሽቀንጥሮ ጥሎ ወደ ትቢያ ቀላቅሏቸዋል። ዛሬ ደግሞ አሁን ያለውን አገር አጥፊ የወያኔን አገዛዝ እየተፋለመና እየታገለ በሚገኝበት ወቅት፣ ይህንን ትኩረቱን ለመስረቅ ታሪኩን አዛብተውና ያልሆነ መልክ ሠጥተው በማቅረብ ሊነገሩት ተነሥተዋል። ለምን...? ማንንስ ለመጠቀም...? ወያኔን...?

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ! የዚህ ጽሁፌ መነሻ፣ ሰሞኑን የጀርመን ድምፅ ራዲዮ ጋዜጠኛ የሆነው ነጋሽ መሐመድ፣ እሁድ ዕለት ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም (July 4/2010) *"የኢትዮጵያ ፖለቲካና የልኂቃና ሚና!* በሚል ርዕስ ሥር ሶስት እንግዶቹን ጋብዞ፣ የ40 ዓመቱን የትግል ጉዞ ወደኋላ ተመልሰው እንዲገመግሙለት ውይይት አስከፍቷል። የጀርመን ድምፅ ራዲዮ ጋዜጠኛ ነጋሽ መሐመድ፣ ይህንን የ40 ዓመቱን የትግል ጉዞ እንዲገመገሙለት የጋበዛቸው ሰዎችን ስብጥር ላስተዋለ ደግሞ (በተለይም የ2ቱ ግለሰቦች) ማንነት ሲጤን አጠያያቂ ከመሆኑም

በላይ፣ እነኝህ 2 ግለሰቦች በዚህ የ40 ዓመት የትግል ጉዞ ሂደት ወስጥ፣ ሠልፋቸው የትና ማን ጋ ቆመው እንደነበር ሲፈተሽ፣ የዚህ ውይይት አቅጣጫና ግብ ምን ሊሆን እንደሚችል፣ ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ይህ ብቻ አይደለም። ነጋሽ መሐመድ ይህንን ፕሮግራሙን ሲሠራ ውይይቱን ለማስጀመር መግቢያውን እንዲህ አዘጋጅቶታል።

> *በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የያዙት ልኂቃኑ እንደሆኑ ይታወቃል። ከባለፉት ሥርዓቶች ጀምሮ እነዚህ ልኂቃን አሁን ኢትዮጵያ ለምትገኝበት ችግር በአንድም ይሁን በሌላ ተጠያቂ ናቸው።*

ይላል። ይህ በዚህ እንዳለ ነጋሽ መሐመድ ወደ ኋላ ይመልሰንና ያለፈውን የ40 ዓመት የትግል ጉዞ፣ ላይ ላዩን ነካክቶ የደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ የፈፀመውን፣ ትውልድን የፈጀ አሰቃቂ ዕልቂትን አንሸዋሮ በማቅረብ፣ የአገዛዙን የጭካኔ በትር በሁለት ደርጅቶች መካከል የተካሄደ አስመሎ ለማሳየት ሞክሯል። ሁለቱ ድርጅቶች ይላል ነጋሽ፥ ሁለቱ ድርጅቶች አንድ ዓይነት ርዕዮትና አቋም የሚከተሉ ሆነው ሳለ በቃላትና በፊደል ኳኳታ እስከ "መገዳደል" ደርስዋልም ይላል ጋዜጠኛው። ነጋሽ መሐመድ ይህንን ጉዳይ እንዲህ አድርጎ ሲያቀርበው ብዙ አልተጨነቀበትም። *"ብልጦች የማይሄዱበትን መንገድ፣ ሞኞች ይሮጡበታል"* እንደሚባለው መሆኑ ነው።

ለመሆኑ ሐቁ ይሄ ነው...? ይህንን መሰል የተዛባ መልዕክት ዛሬ ታሪኩን ለሚያውቀውና በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥም አስቃቂውንና ከባዱን የመከራ ገፈት ለተጋፈጠ ህዝብ እንዲህ ብሎ ማቅረብ የኢትዮጵያን ህዝብ መናቅ አይሆንም...? በመሠረቱ ነጋሽ መሐመድ ሊያስጭበጥ የፈለገው የዚያ ጊዜው ፍጅት መንሥኤ፣ እንደርሱ አባባል በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል *"ሳባደር እና ወዝ አደር፣ እናሸንፋለን እና እናቸንፋለን"* በሚል የቃላት ሽኩቻ የተቀጣጠለ እልቂት እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ  እውነታውን ከአፈር ደባልቆ ታሪክን ያውገረግራል። የፍጅቱን ባለቤትና ዋና መሐንዲስ ደርግ/ኢሠፓንም ሳያነሳ እንዲያውም ያን ጨካኝ አገዛዝ ነፃ ሊያደርገው ሲሞከር ይታያል። ያገሬ ሰው *"ጓደኛህን ንገረኛና ማንነትክን ልንገረህ"* ይላል። ያ! ሰው በላ የደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ ከእንግዲህ ላይመለስ በሕዝብ ትግል ወደ ትቢያና መቃበሩ ወረዶ እያለ፣ ነጋሽ መሐመድ ለወደቀ ሥርዓት ይሸቆጠቆጣል። ግን ለምን...? እውነት ነው ዛሬ እውነትን አቁስለው ሐሰትን ያነገሡ በዝተዋልና፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን የተካው ለገሠ ዜናዊ ራሱ፣ በግንቦት 1997 ዓ.ም ህዝባዊ ምርጫ ላይ፣  *"ድምፃችን ይከበር"* ብለው ሠልፍ በወጡ ወጣቶች ላይ ለፈፀመው የግድያ ወንጀል፣ ተጠያቂ ያደረገው ተቃዋሚዎችን ነው።  የተገደሉ ወጣቶችንም *"ቦዞኔዎችና ባንክ እንዲዘርፉ ተቃዋሚዎች ያሠለፏቸው ሌቦች ናቸው* ብሎ መሳለቁም አይዘነጋም።

ነጋሽ መሐመድ አሁን እንዳለንና  ሌሎችም በተደጋጋሚ ሊነግሩን እንደሚሞክሩት፣ እልቂቱ እውነት *በ'ቻ' ና  በ'ሻ'* ፊደል የተነሳ  ነበርን...? ለመሆኑ እነሱ እንደሚሉት በነዚህ ቃላትና ፊደል *"ታላለቁ"* በማለት የሚያስተጋቡትና ሲያስተጋቡ መኖራቸው፣ የነበረውን እውነታ ይቀይረዋልን ? ወይስ እነኝህ ሰዎች ይፈሩ ይሆን...? ካልሆነ እውነታን ስለ አውገረገሩ፣ ታሪክ ተኖ አይጥይፋም። በተጨማሪም እንኳንስ ዛሬ ያ ጨካኝ አገዛዛ ወደ መቃበሩ ወርዶ እያለ ቀርቶ፣ በህይወት በነበረት በዚያ በ 17 ዓመቱ የጭካኔ አገዛዝ ዘመኑም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት በሆነው ራዲዮና ቴሌቭዥን፣ የአገዛዙ  ልሣን ብቻ ሆነው ሲያገለገሉ በቆዩት... አዲስ ዘመን ጋዜጣና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያን ሄራልድና በመሳስሉት የአገዛዙ የፕሮፓጋንዳ መሣሪዎች ወዘተ.... ተጠቅሞ የነዛው ፕሮፓጋንዳ ሀቁን ሊቀይረው አልተቻለውም። ይልቁንም በባዶው ሜዳ ላይ ሲቅራራ ኖሮ መውደቂያውን አፋጥኖ ወደ ውደቀቱ ተጓዘ እንጅ። ያ ሥራዓት ጨካኝ ነበር፤ ያ አገዛዝ አምባገነንና ሰው በላ ነበር። በዚያ የግፍ ዘመን  ብዙ አስቃቂ ነገሮች ተፈጽመዋል። ለአብነት ያህል *"የእሰር ቤቱ አበሳ፥ በታላቁ ቤተ-መንግሥት (ከ1966-1974 ዓ.ም"* በተባለው ዕርእስ ሥር አቶ

አበራ ጀምበሬ በ200 ገጽ መጽሐፋቸው ውስጥ በደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ ወቅት፣ ፍትህን በማጉደልና በማዛባት፣ ያለምንም ሕጋዊ አካሄድ/አገባብ የታሠሩ፣ ያላግባብ ታሥረውም እስር ቤት ውስጥ የሞቱ፣ እስር ቤቱ ውስጥ በህመም የተሠቃዩ፣ ፣...ወዘተ ስዎችን ሥም ዝርዝር (ማንነታቸውን ገላጭ በሆነ መልክ) አካተው ፅፈዋል። ከ500 በላይ ከነበሩት እስረኞ ውስጥ፥ ለረጅም ጊዜ ታስረው የተፈቱ፣ እንደገና ተመልሰው የታሰሩ፣ የተገደሉ፣ በእስር ቤት ውስጥም በአስቃቂ ሁኔታ ተሰቃይተው የሞቱትንም አካተው፣ በመጽሃፋቸው ውስጥ በዝረዝር አሥፍረዋል። እና ነጋሽ ዛሬ ሊነግረን እንደሚፈለገው፣ እነዚህ ሁሉ ቁጥራቸው ከ 500 በላይ የሆኑ (በዚያ አገዛዝ ዘመን ታሠረው የነበሩ ናችውና) ሰዎች በሙሉ፣ የሁለት ድርጅቶች አባላት የነበሩ ናቸውን....? ለመሆኑ እነኝህ እስረኞች በሙሉ፣ ካለምንም የፍትህ አካሄድ ሰዎችን በሚያሳድድ፣ በሚያስር፣ አስሮም በሚያስቃይና የሚረሽን ሥርዓት ሰለባዎች ናቸው....? ወይስ እነዚህም በ'ሸ' እና በ'ቻ' የተነሳ የተጋደሉ፣ የተበደሉ እስረኞች... ?

*"ሽብር በኢትዮጵያ "*

*ያ!* የትናንቱ የደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ ዘመን... የሰው ልጅ አውሬነቱ በአደባባይ የታየበት፣ የሰው ልኩ የተፈተነበት፣ የኢትዮጵያ ሥነ ደንብ ተጥሶ እናት የልጇን እርም የበላችበት፣ በልጇ ሬሳ ላይ እንድትዘፈን የተደረገበት፣ ለልጇ ሞት ለቅሶ እንዳትቀመጥ የተከለከለችበት፣ አስከፊና አስቃቂ ሥርዓት ነበር። ያ ዘመን! በስንት ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በቀይ ሽብር በየአውራ ጎዳናው ላይ ሬሳቸው ተረፍርፎ፣ ሬሣቸውም በየአውራ ጎዳናው ላይ ተስጥቶ፣ ሕዝብ የልጆቹን ሬሣ የተመለከተበት፤ ወላጆች ልጆቻቸው በጥይት ተደብድበው መገደላቸው አልበቃ ብሎ፣ ለተገደሉበት የጥይት ዋጋ 100 ብር እየከፈሉ ሬሳ የገዙበት፣ አስቃቂው የደርግ/ኢሠፓ ዘመንና ሥርዓት ነበር። ያ! ሽበር ሁሉንም የህበረተሰብ ክፍል የነካና ቤቱን ያፈረሰ፣ ቤተሰቡንም የበተነ፣ በአጠቃላይ ህዝብን፣ በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር ጥቁር ከል ያለበሰ አስቃቂና በታሪካችን ጥቁር ነጥብን ያስመዘገበ ነው። ያ ሽበር ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክትና ዓላማውም ለሟቹ ሳይሆን፣ ቋሚው እንዲርድና ለአንዴም ለሁሌም ፀጥ፣ ለጥ ብሎ እንዲገዛና በሰቀቀን እና በፍርኃት አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር ታስቦ የተደረገ ክፉና የሰቆቃ ዘመን ነው። ደርግ/ኢሠፓ እንደ ሀገር በመላ ኢትዮጵያ ላይ ሽብርን "ሕግ" አድርጎ በነጋሪት ጋዜጣ አስደግፎ ሲያውጣ፣ ህዝብን በአደባባይ አቁሞ፣ ቀይ ቀለም በጠርሙስ ሞልቶ በህዝቡ ፊት ደንፍቶ ሲያፈስ፣ የሽብሩን ሕግ - መኃላ መፈፀሙን የሚያሳይ የሽበር መለከት መንፋቱ ነበር። ሐቁ እና መራራው እውነት ይሄ ነው።

ታዲያ የዚያው ዘመን የኢትዮጵያ ራዲዮ ጋዜጠኛ ባልደረባ የነበረው ነጋሽ መሐመድ፣ ያ አስቃቂ ፍጅት የተካሄደው "*በቃላት እና በፊደል ምርጫ"* ሽኩቻ ምክንያት እንደሆነ አስመስሎና በዚህ ደረጃም አውርዶ ወይም ዝቅ አድርጎ ሊያቀረብ መሞከሩ፣ በእውነቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተሳሰብና ህሊና ባጠቃላይ፣ የትውልዱን ደግሞ በተለይ አሳንሶ ለማቅረብ የተደረገ ለመሆኑ አያጠያይቅም። ግን እኮ ገፈቱን የተጋፈጥው ህዝብ አለ ይሰማል፤ ስምቶም ይታዘባለና ትርፉ ራስን ከማስገመት ውጭ የነበረውን ሁኔታ አይቀይረውም። ስለዚያ ትውልድ ደግሞ መነገር ካለበት አዎ! *ያ! ትውልድ!*

- ከጊዜው ቀድሞ የሄደና የበሠለ፣ ለሀገሩ ኢትዮጵያም ቀናዒና ደጉን የተመኘ፣ ለሚያምንበትና ላመነበት ዓላማም ተግቶ የሚሠራና የሠራ፣ አምኖ ለሚጠጋው ወዳጁ ደግሞ ሥስ ልብ ያለው፣ ለጠላቱ በእርግጥም የሚፋጅ አለሎና ያመረረ፣ ቆራጥ ትውልድ እንደነበር ጠላቶቹ ሁሉ ሳይቀር የመሠከሩለት ሐቅ ነው።

- ያ! ትውልድ ብስለቱ፣ የአስተሳሰብ አድማሱ፣ የጠለቀ የፖለቲካ ግንዛቤው፣ የማንበብ ፍላጎቱ፣ በጥልቀት የመከራከርና ኃሳቡን የመግለፅ ችሎታው፣ የተደነቀና ዓለምን የሚያይበት ዕይታውም ሰፊ የነበረ ነው፤

- ያ! ትውልድ እጅግ ትሁት፣ አገሩን በጣም የሚወድ፣ ለሀገሩና ለሕዝቡ ፍቅር ሲል ደግሞ፣ ለሕይወቱ እንኳን ያልሳሳ፣ ሞትን የናቀና በተግባርም ከሞት ጋር እሽቅድምድም ይዞ፣ ሞትን ሞቶ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሳየ፣ ያሠመሰከረ፣ አይበገሬ ትውልድ ነው፣

- ያ! ትውልድ እንዳዛሬዎቹ ፖለቲከኞች በየመደረኩ ልታይ ልታይ የማይል፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ትንሸ፣ ትልቁን ሴት፣ ወንዱን፣ የዚያ አገር ልጅ፣ የዚያ መንደር ልጅ፣ ሳይል፣ ዘርና መንደር ሳያውቅና ሳይቆጥር፣ ዜጋን በዜግነቱና በሰውነቱ ብቻ በዕይታው ውስጥ አስገብቶ የሚመለከት፤ ለተቀረው የዓለም ሕዝብ ሁሉ ደግ ደጉንና በጎውን ሁሉ የሚያስብ ቅን ትውልድ ነበር/ነውም።
- ያ! ትውልድ ሃሳብ(idea)ን አፍላቂ እንጅ፣ ኃሳብን ነጣቂ አልነበረም፤ ያ! ትውልድ ድምፁ የማይሰማ፣ ተግባሩ ግን የሚጮህ የሚስተጋባ ትውልድ ነበረ ነውም። ያ! ትውልድ የሄንን ሠራሁ፣ ያንን አድረግሁ ሳይል፣ ሠርቶ ያሳየና የሚያሳይ ትውልድ ነው

- ያ ትውልድ፣ "እኔ፣ እኔ፣ እኔ፣" ማለትን የማይሻ፤ እኛነትን ግን ማዕከል የሚያደርግና የሚያጎላ፣ ከእኛነት ማዕከል ውስጥም በየትም ቦታ ቀድሞ የሚገኝ፣ ህዝብ በሚሰባሰብባቸው በየትኛውም አደባባዮች ተደብቆ የማያውቅ፣ ቀና ማለትን እንጅ ማቀርቀርን የማይወድ፣ ከሕዝብ ጀርባም የማይደራደርና ለድርድር የማይቀመጥ፤ ለሁሉም/ለማንኛውም ሰው ለተበደለ፣ ለተገፋ፣ ለአዘነ፣ ፍትህ ለተዛባበት፣ ፍትህን ላጣ መከራ ለደረሰበት ሁሉ የሚጮህ፣የሚያልቅስ፣ የሚያነባ።

- ያ! ትውልድ ከጅምሩ ሲነሣ፣ ዕይታው የዛሬን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም አማትሮና አርቆ የሚመለከት፣ ከዚያ ባሻገርም መጭውንም ቀደሞ የሚያይ፣ የሚጠቁምና አቅጣጫን የሚያመላከት ብሩህ፣ የጨለመና ድንግዝግዝ ያለ ሲመስል ቀደሞ ሻማ የሚለኩስ፣ ልበ ሙሉና አይበገሬ ትውልድ ነበር/ነውም።

- ያ! ትውልድ ትንሽ ተናግሮ ብዙ የሚደመጥ፣ የሚሰማ፤ የተናገረውም የሚይዝለትና ከመሬት የማይወደቅ፣ ራዕዩም ያለረጀና የማያረጅ፣ በየጊዜው የሚታደስ፣ ባለ ራዕይ ትውልድ ነው።

- ያ ትውልድ በጠላቶቹ በጣም የሚፈራ በአንፃሩም የሚከበር፣ ጠላትና ወዳጁንም አበጥሮ የሚያውቅ፣ ጠላቱን ደካማ ነው ብሎ የማይዘናጋ፣ ጠንካራ ነው ብሎም የማይሸበር.....ነገሮችን በጥልቀት የሚያይና የሚመረምር፣ በአጋጣሚዎች የማይሸበር፣ ሁሉንም በሚዛን ለማዬትና ለመመለከት የሚሞከር፣ ሁሌም ለመማር የተዘጋጀ ከህዝብም ብዙ ትምህርት የቀሰመ... በሕዝብ አሸናፊነትን ጥርጥር የማይገባው ...ወዘተ ትውልድ ነው።

የደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ ይህንን የመሰለ ትውልድ በቀይ ሽበር ቀጥፎል፣ ደም እንደጎረፍ አፍስሷል፤ ያ አገዛዝ ይህንን መሰል ጭፍጨፋ አካሂዶ ያን መሰለ ትውልድ በመጨረሱ፤ እነሆ ዛሬ እንደ ሀገር ለደረስንበት ውርደትና ኢትዮጵያን ለወያኔ አሳልፎ ሲሰጥ አስቦበት፣ እኔ በሥልጣን እስካለሁ የእኔ ናት፣ እኔ እስከሌለሁ ግን እንድፈለገች ትሁን....ብሎ "እኔ ከሞትክ ሰርዶ አይብቀል" ዓይነት፣ ሕዝብንና ሀገርን ከፈቶ ለጠላት አስልፎ ሰጥቷል፣ ይህ በታሪክ ቦታ የተመዘገበ እውነት ነው። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂው ራሷ አምባገነኑ አገዛዝ ደርግ/ኢሠፓ እንጂ፣ የአገዛዙ ሽብር ሰለባ የሆነውና የነበረው ኢሕአፓ ከቶ ሊሆን አይችልም።

እንዲያው ለነገሩ በዚያ የጭካኔ አገዛዝ ወቅት ሽብሩ በዚህ ብቻ ያቆመ ነበር..? ከቀይ ሽብሩ በኋላስ የነበረው ሁኔታ ምን ይመሰል ነበር። ያ ዘመን እንዴት ሊረሳ ይችላል ...?

*<u>"ብሔራዊ ውትድርና"</u>*

ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላ ወጣቶች ለ *<u>"ብሔራዊ ውትደርና"</u>* እየተባለ በግዴታ ከእናታቸው ጉያ እየተነጠቁ ለጦርነት አልተማገዱምን ....? ስንቶቹ ወላጆችስ ልጆቻቸው ከትምህርት ገበታቸው ታፍሰው የት እንደደረሱ ሳያውቁ፣ እስካሁን ድረስ በመሪር ኃዘን እየተወዘወዙ ያሉና እድሜያቸውን ሙሉ በእንዲህ አይነት ሁኔታ እየገፉ መሆናቸው እንዴት ይዘነጋል? *<u>"ብሄራዊ ውትድርና"</u>*፣ *<u>"ነፃ እርምጃን "</u>* የይርጋ ዱባለ *<u>"የፍየል ወጠጤ ሽለላና ቀረርቶ"</u>* ፥ *<u>የጋዜጠኛ አሰፋ ይርጉ ድምፅ</u>* ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰቀቀን እንቢልታ ሆኖ መኖሩ ተረስቷል ከሚል ይሆን?

በመሠረቱ የዚያ የደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ ዘመን፣ አስከፊና አስቃቂ እንደነበር ለመደበቅ፣ ያን አስቃቂ ፍጀትም ሽፋፍኖና አድበስብሶ ለማለፍ ማሰብ፣ እንዲሁም ውኃ ሊቋጥር በማይችል እንቶ ፈንቶ አዛብቶ ለማቅረብ መሞከር፣ ኃላፊነት የጎደለውና የጋዜጠኝነት ሙያንም ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው። በመሆኑም እንዲህ ዓይነት የተዛቡና ከሃዲዱ የወጡ የታሪክ ብረዛዎችን ማስተካከልና በጊዜ ቦታ ቦታቸውን እንዲይዙ ማድረግ፣ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት ነው ባይ ነኝ። ዝምታ አገራችንንም ያሳጣናልና።

ልብ በሉ! ትናንትና "ኢትዮጵያ የ100 ዓመት ታሪክ ብቻ" ያላት ናት፤ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር "አማራው" ቀጥቅጦና አቅልጦ የሠራት ሸክላ ወይም ገል ናት፤ ኢትዮጵያዊነት ማለት በማንነታቸው፣ በትውልድ መንደራቸውና ቀያቸው የሚያፍሩ ሰዎች የሚደበቁበት "የነፍጠኞች ዋሻ" ነው እያሉ ይህንን የዘቀጠና ውሉን የሳተ አባባልቸውነም እውነት ለማስመሰል "የአማራ ህዝብ ከየት ወዴት" ብለው የፃፉልን መፅሐፍ በእጃችን ያለ ምስክራችን ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ታሪክ ተዛብቶ ሲቀረብ በዝምታ ማሳለፍ ከመረጠ፣ እንደ ሀገር የቆመበተን መሬት ቀስ በቀስ እየናደ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ታሪኩን ነቅቶ በመጠበቀ ከታሪክ ቀበኞች ማዳን ይጠበቅበታል። ወያኔ ከገባ ጊዜ ጀምሮ በ20 ዓመቱ ጉዟችን ውስጥ፣ መሬታችን ልትሸከመው የማትችል... ጆንያ ሙሉ ሐሰት ከኢመንት እውነት ጋር አጨቀው፣ ስንት መፅሐፍት ተፅፈው እየቀረቡለን እንደሆን እያየን ነው። ወያኔስ አዲስ አበባ እንደገባ ብዙ ሳይቆይ አይደል እንዴ *<u>"ተራራውን ያነቀጠቀጠ ትውልድ"</u>* ብሎ መፅሐፍ አትሞ የሸጠልን!?

ስለዚህ ክቡር ጋዜጠኛ! እንደዚህ ዓይነት፣ ወቅታቸውን ያልጠበቁ፣ በአንፃሩም ለወያኔ ብቻ የሚጠቅምና የሚያገለግል እሰጣ ገባዎችን በአሁኑ ሰዓት መክፈት፣ ትግሉን የሚያጠራ ሳይሆን የሚያደፈርስ፣ ወያኔንም የሚጠቅምና የኢትዮጵያን ሕዝበ አበሳ የሚያራዝም የሞኞች ዓይነት ጨዋታን ለኋላ ብናቆየውስ። *<u>"ብልጦች የማይሄዱበትን መንገድ - ሞኞች ይሮጡበታል!</u>*

ዳሩ ግን <u>"የጀርመን ድምፅ ራዲዮ"</u> ማለት ስሙ እንደሚያመላክተን የጀርመን ህዝብ ድምፅ ማለት ሲሆን፣ አገልግሎቱም የጀርመንን ህዝብ ጥቅም ማስጠበቅ፣ የጀርመን መንግሥት አቋምንም የሚያንፀባረቅ ማለት ነው። ተሳሳትኩ?

## የሕዝብ ትግል ያቸናፋል! የታሠሩ የፖለቲካ እሥረኞች በሙሉ ይፈቱ!
## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን

julay 10/ 2010